Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የኮሌጅ፣ የስራ እና የማህበረሰብ ዝግጁነት መንገድ

MCPS ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና አስተማሪዎች የተማሪን ስኬት ለማረጋገጥ አብረው እንዲሰሩ ለመርዳት አዲስ መመሪያ አዘጋጅቷል።

**የኮሌጅ፣ የስራ እና የማህበረሰብ ዝግጁነት መንገድ እያንዳንዱ ተማሪ የሚፈልገውን ድጋፍ ማግኘቱን ለማረጋገጥ የተማሪዎችን ጥንካሬዎች እና ማሻሻል ያለባቸውን ለመለየት ይረዳል።**

እንዴት እንደሚሰራ እነሆ:-

- ተማሪዎች ወደ አዲስ የክፍል ደረጃ፣ ኮሌጅ ወይም የስራ ግብረሃይል ከመሸጋገራቸው በፊት ያሉትን ማናቸውንም የትምህርት ክፍተቶች ለማሟላት ከዚህ በታች የተገለጹት ወሳኝ ክንውኖች “milestones” ተግባር ላይ ይውላሉ።
- ወላጆች ልጆቻቸው እነዚህን ልዩ መመዘኛዎች ማሟላት ወይም አለማሟላታቸውን የሚገልጽ መረጃ ይደርሳቸዋል።
- የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ለተማሪው(ዋ) እንዲሳካ የሚረዳበትን ከሁሉ የተሻለውን መንገድ ለመወሰን አብረው ይሰበሰባሉ።
- ከአካዳሚክ መመዘኛዎች በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለሚኖራቸው ሕይወት ለማዘጋጀት ዋና ዋና ብቃቶችን እና ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እድል ይሰጣሉ።

(በዚህ ሰነድ ውስጥ ስለተጠቀሱት ቅኝቶች ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት የቃላት መፍቻውን ይመልከቱ)



# አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

## መዋእለ ህጻናት

እርከን: **ቀዳሚ የሊተርሲ ችሎታ**

| ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ? | ይሄ የሚለካው እንዴት ነው? | አስተማሪህ(ሽ)ን መጠየቅ የምትችለ(ይ)ው ምን አይነት ጥያቄዎችን ነው? |
|---|---|---|
| ጥናት እንደሚያሳየው በልጅነት ጊዜያቸው ጠንካራ የሊተርሲ ክህሎት ያዳበሩ ልጆች በትምህርት ዘመናቸው ሁሉ የተሻለ የትምህርት ውጤት አላቸው።<br>ፊደል ለይቶ ማወቅ፣ የሚያዩትን ቃላት መገንባት፣ ማንበብ እና መጻፍ የመሳሰሉ ክህሎቶችን መማር እና ለወደፊት የትምህርት ስኬት መሰረት ይጥላሉ | አስተማሪዎች የልጁን/የልጅቱን የማንበብ ችሎታ"DIBELS" በሚባል ፈተና ይለካሉ።<br>ፈተናው በትምህርት አመቱ ሶስት ጊዜ ይሰጣል፣ ፎል፣ ዊንተር፣ እና ስፕሪንግ<br>ልጆች 420 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ "የተቀናጀ ውጤት" ሊኖራቸው ይገባል | በውጤቱ መሠረት ልጄ ተጨማሪ ድጋፍ ወይም ማሻሻያ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት የትኞቹን የንባብ ዘርፎች ነው?<br>የልጄን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ?<br>ትምህርት ቤቱ ማንኛውንም የማንበብ ችግር ለመፍታት ምን ስልቶችን እየተጠቀመ ነው? |

## 3ኛ ክፍል

እርከን: 3ኛ ክፍል ንባብ

| ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ? | ይሄ የሚለካው እንዴት ነው? | አስተማሪህ(ሽ)ን መጠየቅ የምትችለ(ይ)ው ምን አይነት ጥያቄዎችን ነው? |
|---|---|---|
| 3ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ በደንብ ማንበብ መቻል አስፈላጊ የትምህርት መለኪያ ነው። ለወደፊቱ የትምህርት ስኬት መሰረት ነው። በዚህ ወቅት ልጆች ከመማር ወደ ማንበብ እና ከማንበብ ወደመማር ይሸጋገራሉ። | ሁሉም 3ኛ ክፍል ተማሪዎች "MAP-R" የሚባል ፈተና ይወስዳሉ።<br>ተማሪዎች 600L የቃላት 'lexile' ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ሊኖራቸው ይገባል። | ለልጄ እድሜ ተስማሚ የሆኑ መጽሃፎችን ማስጠት ይችላሉ?<br>ልጄ የዲስትሪክቱን መለኪያ ሚዛን ያሟላል/ታሟላለች?<br>ቤት ውስጥ ተማሪዬን ለመደገፍ ምን ማድረግ እችላለሁ?<br>ትምህርት ቤቱ ማንኛውንም የማንበብ ችግር እንዴት ይፈታል? |

## 4ኛ እና 5ኛ ክፍል

እርከን: በሂሳብ እና እንግሊዝኛ/ቋንቋ ስነጥበብ በቂ ችሎታ

| ይህ ለምን አስፈላጊ ሆነ? | ይሄ የሚለካው እንዴት ነው? | አስተማሪህ(ሽ)ን መጠየቅ የምትችለ(ይ)ው ምን አይነት ጥያቄዎችን ነው? |
|---|---|---|
| 4ኛ ክፍል ጀምሮ ተማሪዎች የሚማሩት እያነበቡ ነው። የሂሳብ ትምህርትን ከመሳሰሉ ሌሎች የትምህርት ዘርፎች ያገኙትን ችሎታዎች በጥልቀት ለማሰብ እና ችግሮችን ለመፍታት ይተገብራሉ። | 4ኛ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና ፕሮግራም (MCAP) ፈተና ይወስዳሉ።<br>ፈተናዎቹ የሚሰጡት በስፕሪንግ ወቅት ነው።<br>ተማሪዎች 3 ወይም ከዚያ በላይ ውጤት ማምጣት አለባቸው። | ልጄ አሁን ባለ(ች)በት የክፍል ደረጃ ምን የተለየ የሊተርሲ እና የሂሳብ ክህሎቶች ይጠበቃሉ?<br>ትምህርት ቤቱ ምን ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጣል?<br>የስቴት ደረጃዎችን ለማሟላት ወይም ከዚያ በላይ ውጤት ለማምጣት የልጄን የሊተርሲ እና የሂሳብ ክህሎት ማዳበር በቤት ውስጥ እንዴት መደገፍ እችላለሁ?<br>ልጄ የስቴት የሊተርሲ እና የሂሳብ ደረጃዎችን እንዲያሟላ/እንድታሟላ ለመርዳት የትኞቹ ስልቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ? |

## የምዘና መዝገበ ቃላት

DIBELS - መሠረታዊ ቀደምት የሊተርሲ ችሎታ ለውጥ ጠቋሚዎች የማንበብ ክህሎቶችን የመፈተን እና የመገምገም ሂደቶች እና እርምጃዎች ስብስብ ነው። ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ ስምንተኛ ክፍል ቀዳሚ ሊተርሲ እና ቀዳሚ የማንበብ ክህሎት እድገት ስጋትን በመደበኛነት ለመለየት እና ለማስተካከል የተነደፉ አጫጭር (አንድ ደቂቃ) የቅልጥፍና መለኪያዎች ናቸው።

MAP-R -የአካዳሚክ ግስጋሴ-ንባብ መለኪያዎች (MAP-R) በተለያዩ የንባብ ስኬት መስኮች የተማሪን የክህሎት ደረጃ ይገመግማል። እነዚህ በርካታ ምዘናዎች አስተማሪዎች በጊዜ ሂደት የንባብ እድገት ደረጃን ለመለካት ያስችላቸዋል።

Lexile - Lexile ሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ የንባብ ችሎታ ማዕቀፍ ነው። ምዘናዎቹ የበለጠ ትክክለኛ የንባብ ግንዛቤ ችሎታን ያመለክታሉ። MCPS የሚጠቀምበት "Lexile Reader Measure" መለኪያ፣ የተማሪን የንባብ ችሎታ በሌክሰይል ሚዛን/Lexile scale ያሳያል።